www.fsc.gov.et

የሰ/መ/ቁ. 132055

ጥቅምት 8/2009 ዓ.ም.

ዳኞች- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች - አቶ አህመድ ደርባቸው ጠበቃ ሬድዋን ከማል

ተጠሪ - ፌዴራል ዐቃቤ ህግ- ሙሉ ተስፋ ከበደ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካች በተጠሪው በቀረበባቸው የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ጋር ተያይዞ ጉዳዩን የያዘው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ የሚሰማበት ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠቱና ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) የዋስትና መብት ተጠብቆላቸው እንዲከራከሩ ለፍርድ ቤቱ በማመልከታቸው ነው፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ተቃውሟል ተጠሪ በመቃወሚያል አመልካች ቀደም ሲል በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት ወንጀል ተከስሰው የሦስት ወር እስራት በ2 ዓመት ገደብ የተፈረደባቸው ሲሆን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሌላ የቼክ ማጭበርበር ወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ ስለዚህ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) መሠረት የዋስትና መብት ጥያቄአቸው ውድቅ ሊሆን ይገባዋል ሲል ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ቀደም ሲል የቅጣት ገደባቸው ሳያበቃ አሁን ከተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ የሆ ወንጀል ፈጽመው የተቀጡ መሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) መሠረት ሌላ ወንጀል ይፈጽሙ ይሆናል ተብሎ የሚገመት በመሆኑ የዋስትና ጥያቄው አልተቀበልነውም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ወስኖአል፡፡

አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ን በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውታል ይታረምልኝ ሲሉ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ቀደም ሲል የተቀጡበት ወንጀል በዚህ መዝገብ እያከረከረ ካለው የወንጀል ክስ ጋር የተለያየ ሆኖ እያለ በድጋሚ በተመሳሳይ ወንጀል ተከስሷል መባሉ አለአግባብ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አመልካች በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ቢደረግም እዚያው ሆነው የቼክ ማጭበርበር ድርጊት ከመፈጸም የሚያግዳቸው ነገር እንደማይኖር፣ ይልቁንም በዋስ ተለቅቀው ቼክ እንዲያንቀሳቅሱ መከልከሉ አማራጭ መሆኑን ገልጸው በዋስ የመለቀቅ ሕገመንግስታዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በዋስ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ሊፈጽሙ የሚችል ስለመሆኑ ግምት ሊያስወስድ የሚችል ባህርይ ወይም የነገሮች ሁኔታ ሳይኖር የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 67 (ለ) ን በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ዋስትና በሕገመንግሥቱ ዕውቅና ያገኘ መብት ቢሆንም በሕግ ሊገደብ እንደሚቻል የታወቀ ነው ብሏል፡፡ አመልካች ከዚህ ቀደም በቼክ አታላይነት ወንጀል በብር 5000 መቀጮ የ3 ወር እስራት በ2 ዓመት ገደብ የተቀጡ ሲሆን አሁንም እንደገና የግል ተበዳይን እምነት በመጠቀም የወጡት ቼክ እንዳይከፈል ሂሳቡ እንዲዘጋ በማድረጋቸው በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት በአንድ ዓይነት የሕግ ድንጋጌ ተከስሰው ቀርበዋል፡፡ አመልካች በዋስ ቢለቀቁ ሌላ ወንጀል ይፈጽማሉ ከሚል ግምት ከዚህ የበለጠ ማሳመኛ ምክንያት ሊኖር አይችልም ሲል ተጠሪ መቃወሚያውን አቅርቧል፡፡ በፍ/ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለትም ተከራክሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በከፍተኛው ፍ/ቤት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍ/ቤት በፀናው ውሳኔ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ያለፈውን የወንጀል ሪከርድ በማየት አሁንም ተመሳሳይ ወንጀል ከመሥራቱ ይቆጠባል ተብሎ አይገመትም በሚል ነው፡፡

ሆኖም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ስር የተደነገገው የዋስትና መብት ገደብ በተከሳሹ ያለፈ የወንጀል ታሪክ ላይ የሚመሠረት አይደለም፡፡ ይልቁንም የድንጋጌው ዓላማ በእጅ ላይ ያለውን የክሱ ሂደት ሊያደናቅፍ ይችላል ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በዋስ የመለቀቅ

www.fsc.gov.et

መብቱን ለመገደብ ነው፡፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ከንዑስ ቁጥሮች (ሀ) እና (ሐ) ጋር በአንድነት ሲነበብ ይገባል ሕጉ የተከሳሹን በዋስ የመለቀቅ መብት እየገደበ ያለው በዋስትና ወረቀት ላይ የሰፈሩትን ግዴታዎች አይፈጽምም ተብሎ ሲገመት ወይም ዋሶችን ሊያባብል ይችላል ወይም ሊያስፈራራ ይችላል ወይም ማስረጃዎችን ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ተከሳሹ ሲገመት ነው፡፡ የቁጥር 67 (ለ) ድንጋጌም ከንዑስ ቁጥሮች (ሀ) እና (ሐ) ጋር በጣምራ ሲነበብ "ሌላ ወንጀል ሊሠራ ይችላል ተብሎ ሲገመት" የሚለው ድንጋጌ ከተያዘው ክስና ከተጀመረው የፍርድ ሂደት ጋር በተያያዘ ጠባብ የሕግ ትርጉም በተጣጣመ መልኩ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

ፍ/ቤቶቹ የተከሳሾችን ያለፈ የቅጣት ውሳኔ ካሁን ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር በማያያዝ በዋስ ቢለቀቅ ተመሳሳይ የቼክ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ግምት በመውሰድ የዋስትና ጥያቄውን አለመቀበላቸው አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍ/ቤቶቹ ተከሳሽ በዋስ ቢለቀቅ በተከሰሱበትን ጉዳይ ለማድበስበስ ማስረጃ ለማጥፋት፣ ወይም ራሱ ለመሰወርና ከፍርድ ለማምለጥ በአጭር የተያዘውን የፍርድ ሂደት ለማደናቀፍ የወንጀል ድርጊት ይፈጸማል ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 67 (ለ) ን የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መወሰናቸው ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 138 (1) ሕጉ በግልጽ ካልደነገገ በቀር ተከሳሹ በፍርድ ዳኝነት በግልጽ እስከአልታወቀ ድረስ የቀድሞ ጥፋተኝነቱ አይገለጽም ሲል ደንግጓል፡፡ ድንጋጌው የተከሳሽን ንጽሕ ሆኖ የመገመት ሕገመንግሥታዊ መብት የሚያመለክት ሲሆን በተጨማሪም ዳኞች የወንጀል ጉዳይ በሚመረምሩበት ጊዜ በተከሳሹ የጥፋተኝነት ሪከሪድ ጫና አድሮባቸው የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይሰጡ ለማድረግ የሰፈረ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ስለአመልካች የቀድሞ የጥፋተኝነት መዝገብ ሲያቀርብ ፍ/ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ መሠረት እንዳልቀረበ በመቁጠር ሊወሰን ሲገባ ሕጉን በመጣስ በአመልካቹ የጥፋተኝነት መዝገብ ላይ በመመሥረት ማከራከራቸውን መወሰናቸውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.fsc.gov.et

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 21/07/2008 ዓ.ም በወ/መ/ቁ. 146424 የሰጠውና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም በቀን 29/09/2009 ዓ.ም በወ/ይ/መ/ቁ. 127657 ያፀናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ዋስትና በማስያዝ በዋስ ተለቅቀው ጉዳያቸውን እንዲከታተሉ ተወስኗል፡፡
3. ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ታዟል፤ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

# ልዩ ልዩ